# <u>ኬሚካል አሊ</u>

እጆችህ ለግጥም ለኮሶ መጋቻ
ይሆናሉ ብለን ባጅተን ስንጫጫ
ተሞኝተን እኛ ሆነን አላዋቂ
ቆመዋል ተባለ እጆችህ ለፈንጂ፡፡
አሊ ሰዒድ የእኛ ገጣሚ ስንልህ
አሊ ፅኑ ታጋይ ከያኒ ስንልህ
የምሳሌ አባት አርአያ ስንልህ
ለካስ ተሞኝተን እኛ አላዋቂ
ላንት ሚበጀው ስም ኬሚካሉ አሊ፡፡
ቲኤንቲ እጆችህ በፈረንጅ ሲያዙ
በድንገት ፍተሻ ዘብጥያ ሊወርዱ
ከም ኬሚካል አሊ ሊወርድብህ ፍርዱ
ማንነትክን አዩ ዕቅጩን ተረዱ
ይቅርታ መጠየቅ አየን ተገደዱ፡፡
ፈንጂውን አላውቀው ብለህ የደረቅከው
ሳንድዊች ነው ጣፋጭ ብለህ የጠየቅከው
ጉራማይሌ ቀልድህ ሶላቶን ያልገባው
በሳቅ አፈንድቶ ሊገለን ከጀለው
አሊ አሊ መሆንክን ለሁሉ ነገርከው፡፡

ሀማ ቱማ